## የኢትዮጵያን እግር ኳስ ስፖርት ታላቅ ኮከብ የመንግስቱ ወርቁን ዕረፍት በተመለከተ ለቀረበው ዜና የማስተካከያ ደብዳቤ

ከአሳየኸኝ

የተዋቂውን የኢትዮጵያአ የኳስ ንጉስ መንግስቱ ወርቁ ዜና ዕረፍት  አስመልክታችሁ የለጠፋችሁት ፎቶግራፍ የ3ኛውን የአፍሪካ ዋንጫ እየተቀበለ ያለው መንግስቱ ሳይሆን ሉቻኖ ቫሳሎ ስለ ሆነ የራሱን ፎቶ ቢሆን ይመረጣል። ሌላው የቀብሩ ሥነስርዐት በትላንትናው ዕለት በለቡ ቅዱስ ገብርኤል (መካኒሳ አካባቢ) እንደተፈጸመና እናንተ እንዳላችሁት በጴጥሮስ ወጳውሎስ አለመሆኑን እንድታርሙት ነው። ለዚህ ጀግና ብሔራዊ የሐዘን ቀን የሚያስፈልገው፣ ሕይወቱን በሙሉ ለሀገሩ የገበረ፣ ለባንድራው ሟች፣ ለሀገሩ ቀናተኛ ነበር። ግን ምን ያረጋል! አሁን ባለው ጎጠኛ ሥርዐት፣ እንዲህ ያለ ቤሔራዊ ጀግና ቦታ ስለሌው፣ እንደማንም ተራ ሰው ዜና ዕረፍቱ በስፖርት ዜና ወቅት ለሕዝቡ ተገልጿል። ምንም የዜና ሽፋን በአግባቡ




አልተሠራለትም። ለሥሙ አደረግን ለማለት ቅንጭብ ቅንጭብ እያረጉ በስፖርት ዜና ላይ ከማቅረብ በቀር።  ወያኔ በገባ በአጭር ጊዜያት ነበር፣ ትግሬን የማይወድ ተብሎ በያኔው መጋዣ ፈረሳቸው በታምራት ላይኔ በተጻፈ ሁለት መሥመር ደብዳቤ፣ ሕይወቱን በሙሉ ካገለገለበት ቤት እንደማንም ተራ ሰው የተጣለው። እግዚአብሔር ነፍሱን ይማር:: ለቤተሰቡና ለስፖርት ቤተስቦች እንዲሁም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጽናቱን ይስጥልን።

**<u>ከዝግጅት ክፍሉ</u>**

አቶ አሳየኸኝ ለላኩልን ማስተካከያ እያመሰገን ለተፈጸመው ስህተት ይቅርታ እንጠይቃለን።